ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
Solidarity Movement for a New Ethiopia

# ለሁለተኛ ጊዜ፡- ለሚመለከታቸው የኢትዮጵያ ጉዳየኞች (Stakeholders) በሙሉ፤

ከሁለት ሳምንታት በፊት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ይመለከተኛል ለሚሉ በሙሉ ወደ ትብብር እንዲመጡ የሚጠይቅ ደብዳቤ መጻፋችን ይታወቃል፡፡ ይህንን ተከትሎም የተለያዩ አስተያየቶችን ስንቀበል ቆይተናል፡፡

ባለፈው ጥሪያችን ላይ በግልጽ እንዳስቀመጥነው የዚህ ጥሪ ዋና ዓላማ ‹‹የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ፣ ይመለከተኛል የሚሉ ጉዳየኞች በአንድ ቦታ ተሰባስበው የአገራችንን ጉዳይ በተመለከተ የሚመክሩበትን መድረክ ለማመቻቸትና መንገዱን ለመጥረግ የሚያግዝ ጉባኤ ለመጥራት›› ነበር፡፡ ይህንንም ጥሪ ለመገናኛ ብዙሐን **(የፓልቶክ ክፍሎችንም ጭምር) ፣ ለፖለቲካ ድርጅቶች ፣ ለአርነት ንቅናቄዎች ፣ ለሲቪክ ድርጅቶች ፣ ለሴቶችንና ወጣቶች ማኅበራት ፣ ለሃይማኖት ድርጅቶች እንዲሁም ለአገር ሽማግሌዎችን እና ሌሎች ለአገራችን ቅን የሚያስቡና ለነጻነቷ የሚታገሉ** አቅርበን ነበር፡፡

የጥሪውም ዋና ዓላማ ሁላችንም በአንድ ጣራ ሥር ተገናኝተን እና ተወያይተን ወደ አንድ ውሳኔ እና ግብ የምንደርስበትን የትብብር ቀን ቅርብ ለማድረግ የነበረ ሲሆን ይህ ትብብር የሚመሠረተውም በሁሉም ጉዳየኞች መካከል ያለው ስትራቴጂያዊ ልዩነት ለጊዜዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁላችንንም በሚያስተባብርና በአንድነት እንድንሠራ በሚያደርገን ጉዳይ ላይ (አንድም እንኳን ቢሆን) መክረን በአንድነት እንድንነሳ የሚያሳስብ ነበር፡፡ በሌላ አነጋገር በዚህ ሁሉን አቀፍ አገራዊ ስብሰባ ከእያንዳንዱ ጉዳየኛ የሚወከል መሪ ወይም ተወካይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰን የነበረ ሲሆን እያንዳንዱ ጉዳየኛ ድርጅት አሁን እየተንቀሳቀሰ ያለበትን ፕሮግራም ወይም ድርጅታዊ መርሐግብር በምንም መልኩ እንዲቀይር ሳይገደድ ከሌሎች ጉዳየኞች ጋር እንዴት አድርጎ በመተባበር እና መልካም ግንኙነት በመመሥረት የሚሠራበትን መንገድ የሚያመቻችና የሚያስተባብር እንደሚሆን በግልጽ አስቀምጠን ነበር፡፡

የጥሪውን ግዝፈት እና የተሰጠውን የጊዜ ገደብ እንዲሁም እያንዳንዱ ጉዳየኛ ከአመራሩና አባላቱ ጋር ተነጋግሮ ለመወሰን ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ግምት ውስጥ በማስገባት **ለሰኔ 23 ፣ 2002 ዓ.ም.** (June 30th, 2010) የሰጠነውን የጊዜ ገደብ ወደ **ሐምሌ 7 ፣ 2002 ዓ.ም.** (July 14th, 2010) ያራዘምነው መሆኑን እንገልጻለን፡፡ ከዚህ በፊት እንደጠየቅነውም አሁንም መልሱ በጽሁፍ እንድታሳውቁን በትህትና እንጠይቃለን፡፡

በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ የምንፈልገው ዋንኛ ነገር ቢኖር ይህንን የትብብር ሃሳብ በቀና መንፈስና ለአገር ከመቆርቆር የመነጨ በመሆኑ ሌሎች የአገራቸው ጉዳይ የሚያንገበግባቸው ሁሉ እንደዚህ ዓይነት ሃሳብ እንደሚኖራቸው እንዲሁም ሥራውን

ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ የጀመሩ ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገመት ፤ ማንኛውም ይህንን ዓይነት የትብብር ዓላማ ለማካሄድ ከሚፈልግ ቡድን ጋር ተባብረን ለመሥራት ሙሉ ፈቃደኛ መሆናችንን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡ ሆኖም ግን ይህ የትብብር ጉባዔ የሚያለያዩንን ጉዳዮች ወደኋላ በመተው በሚያስማሙን ጉዳዮች ላይ በትብብር ለመሥራት እንዲያስችለን የተጠራ እንጂ የስደት መንግሥት ወይም የነጻውጪ ግንባር ለመመሥረት የተጠራ አለመሆኑን በግልጽ ለማስገንዘብ እንወዳለን፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት ጉዳዮች ትብብሩ ከተመሠረተ በኋላ ጊዜውን ጠብቀው በራሳቸው በጉዳየኞቹ የሚከናወኑ ተግባራት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡

ይህንን መልዕክት በተለያዩ የመረጃ አዉታራት ለማንበብ እድል ያገኛችሁ ወገኖቻችን ሁሉ የተደረገዉን ጥሪ በተመለከተ አሰተያየት ብትሰጡን በአክብሮት የምናስተናግድ መሆኑን በትህትና እንገለጻለን። በተጨማሪም ይህ ጥሪ የተላከላቸውን ዝርዝር ለማወቅ የሚፈልጉ ሁሉ ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት መረጃውን ማግኘት የሚችሉ መሆናቸውን በአክብሮት እናስታውቃለን፡፡

ይህ አገራዊ ጥሪ ለነፃነት ሲሉ ክቡር አካላቸዉንና ህይወታቸዉን በሰዉ ወገኖቻችንና ፣ ለዘመናት በመከራና በሰቆቃ በኖረው ሕዝባችን ስም የተደረገ ሲሆን ለዚህም ወገንን የማዳን ጥሪ አፋጣን ምላሽ በመስጠት ሕዝባችን ለዘመናት ሲናፍቀው የኖረውን ነጻነት ዕውን በማድረግ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው የአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም ሊያስገኝ በሚችል ተግባር ሁላችንም ቀና ውሳኔ ለማድረግ እንድንችል ፈጣሪያችን ይርዳን፡፡

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር



ኦባንግ ሜቶ
ዋና ዳይሬክተር
ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

**************************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ* ***የንቅናቄውን የዕርቅ ግብረኃይል*** *በ (reconciliation@solidaritymovement.org) ወይም ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

